# ፓርላማ ዜና መጽሔት

6ኛው የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ ህዳር 25 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 3ኛ መደበኛ ስብሰባ የተለያዩ ረቂቅ አዋጆችንና ሹመቶችን አጽድቋል፡፡

በዕለቱ ምክር ቤቱ ወንጀልን በጋራ ለመከላከል የሚያስችሉ የተለያዩ ረቂቅ አዋጆችን ለዝርዝር እይታ ለህግና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርቷል፡፡

የህዳር ወር ዜና መጽሔታችን እነዚህንና ሌሎች አበይት ምክር ቤታዊ ውሳኔዎች ታስነብባለች፡፡



## ዓበይት ርዕሶች

- ህግ አወጣጥ
- ሹመት

መልካም ንባብ!
ህዳር፣ 2018 ዓ.ም

## 6ኛው የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ ዓመት የስራ ዘመኑ ህዳር 25 ቀን 2018ዓ.ም በአካሄደው 3ኛ መደበኛ ስብሰባ የተለያዩ ረቂቅ አዋጆችንና የብድር ስምምነቶችን አጽድቋል፡፡

*በዚሁ ዕለት ምክር ቤቱ የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011ን ለማሻሻል የቀረበ ረቂቅ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1397/2018 በማድረግ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል፡፡*



*ምክር ቤቱ ረቂቅ አዋጆችን ሲያጸድቅ*

## በዚሁ ዕለት ምክር ቤቱ የተለያዩ ሹመቶችን አጽድቋል፡፡

*በዕለቱ ምክር ቤቱ ክቡር አቶ አዲሱ አረጋን የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር፣ ክቡር አቶ መሀመድ ኢድሪስን የሠላም ሚኒስቴር ሚኒስትር አድርጎ ሹመቱን ያጸደቀ ሲሆን ክቡር አቶ ቢንያም ኤሮን የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ አድርጎ ሾሟል፡፡*

*ሹመታቸው የፀደቀላቸው ተሿሚዎች በምክር ቤቱ ፊት ቀርበው ቃለ መሀላ ፈፅመዋል፡፡*

